ቁጥር OFAGF-06.13/2/25
ቀን 30/06/2012

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤና

የመቐለ ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ሰብሳቢ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡ <u>የመቐለ ዩኒቨርሲቲን የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የዩኒቨርሲቲውን ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 9 ገጽ የኦዲት ሪፖርትና 4 ገጽ የሂሳብ መግለጫዎችን ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከማክበር ከሠላምታ ጋር

መሰረት ዳምጤ
የኦዲት ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተር

ግልባጭ፡- ለመቐለ ዩኒቨርስቲ

(9 ገጽ የኦዲት ሪፖርት፣ 37 ገጽ የኦዲት ግኝቶች የማሻሻያ ሃሣቦች 17 ገጽ አባሪና 1 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርሃ ግብር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የመቐለ ዩኒቨርሲቲ

የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል::

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የዩኒቨርስቲው ሆስፒታል ለጤና ሳይንስ ኮሌጅ የጥርስ ህክምና አገልግሎት የሚውሉ መሳሪያዎች ሀገር ውስጥ ከሚገኙ አቅራቢዎች መሳሪያዎቹ አለመኖራቸው ሳይረጋገጥ በግዥ መመሪያው ከተፈቀደው ግዥ ባለሙያ ውጭ

የህንድ አገር ዜጎች የሆኑ የዩኒቨርስቲው መምህራን ከህንድ ሀገር ገዝተው ስለመጡ በሚል በድምሩ ብር 214,084.97 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ፡

2. ለጽዳት እቃዎች የሚውል ግዥ ሲከናውን የሽያጭ ደረሰኝ መቅረብ ሲገባው የእጅ በእጅ ሽያጭ አባሪ (Attachment Cash Invoice) በማያያዝ በድምሩ ብር 36,149.98 በቀን 21/09/11 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 545799 የሆስፒታሉ ሰራተኛ ለትምህርት ወደ ደቡብ አፍሪካ ለሄዱበት የአየር ቲኬት ደረሰኝ ሳይቀርብ ብር 33,386.00 በጠቅላላ ድምር ብር 69,535.98 ለወጪው የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣

3. ዩኒቨርሲቲው የጥበቃና የጽዳት አገልግሎት ለሶስተኛ ወገን በውል ሲያሸጋግር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ፈቃድ ሳይጠይቅ በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 38,187,204.80 ክፍያ የፈጸመ መሆኑ

4. መንግስት ባዘጋጀው የሠራተኞች የቀን ውሎ አበል ቅፅ መሠረት ሂሳቡ መሞላትና መወራረድ ሲገባው፣ ዩኒቨርሲቲው ራሱ በቀረፀው የወሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅጽ የተወራረደ ሲሆን በአይደር ሆስፒታል በድምሩ ብር 220,061.45 እንዲሁም በጤና ሳይንስ ኮሌጅ በድምሩ ብር 250,735.95 በአጠቃላይ ድምር ብር 470,797.40 ለውሎ አበል የተከፈለ ሲሆን ሰራተኛው ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራት የደረሰበት ሰዓት ባለመገለፁ የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

5. ዩኒቨርሲቲው ለትግራይ ልማት ማህበር የአባልነት ክፍያ በሚል በቀን 21/10/11ዓ.ም በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 1287 በድምሩ ብር 100,000.00 ከመንግስት መመሪያ ውጪ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፣

6. በድምሩ ብር 59,455,074.65 በወቅቱ መወራረድ ሲኖርበት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣

7. በዋናው ግቢ በሂሳብ መደብ 5006 ብር 9,549.26 እና በሂሳብ መደብ 5059 ብር 404,791.46 በድምሩ ብር 414,340.72 በአይደር ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል በሂሳብ መደብ 5059 ብር 129,641.95 በአጠቃላይ ብር 543,982.67 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) በመመዝገቡ የዩኒቨርስቲውን የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ዝቅ እንዲል ማድረጉ፣

8. ከመደበኛ በጀት ብር 2,940,212.59 ለየአርእስቱ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ መደረጉ ታውቋል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች በስተቀር የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ትክክለኛውን ገጽታ ያሳያሉ፡፡

1. ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች(Emphasis of Matters)

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባስተላለፊው የአፈጻጸም መመሪያ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብሎክ በሚደረግ ሂሳቦች ላይ የB እና የD የባንክ ሂሳቦች ብሎክ ተደርገው ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ የሚደረገውን ሂሳብ ፈሰስ መሆኑን ክትትል ማድረግ እንዲሁም የ2012 በጀት ዓመት የሐምሌ ወር የክፍያ ጥያቄ ሲቀርብ ብሎክ ተደርገው ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ የተደረገበትን የባንክ አድቫይስ አያይዘው ማቅረብ እንዳለባቸው የሚገልጽ ቢሆንም የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ የB የባንክ ሂሳቦች ብሎክ ተደርገው ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ ሳይደረጉ በባንክ መግለጫ መሰረት ሰኔ 30/2011 ብር 86,153,188.57 ከወጪ ቀሪ ሚዛን የሚታዩ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል
- ለየአርዕስቱ ከተደለደለው ከመደበኛ በጀት ብር 1,868,213.33 እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 3,400,148.41 በድምሩ ብር 5,268,361.74 ስራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ

2. ሌሎች ጉዳዮች(Other Matters)

ንብረት ፣

2.1. የንብረት አመዘጋገብ፣አያያዝ እና አጠባበቅን በተመለከተ፣

በዋናው ግቢ

የተማሪዎች ምግብ ቤት ዋና ግምጃ ቤት

- የንብረት ወጪ ሞ/22 እና ስቶክ ካርድ ምዝገባ በአንድ ሰራተኛ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑ፣

- በተማሪዎች ምግብ ቤት መጋዘን ውስጥ ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት የሚውሉ ጤፍ፣እርድ እና ሻይ ቅጠል ለብልሽት በተጋለጠ ሁኔታና ለቁጥጥር በማይመች መልኩ ሜዳላይ ተበታትኖ የሚገኝ መሆኑ፣
- ለተማሪዎች ምግብ ማብሰያ አገልግሎት የሚውል ወጥ መስሪያ በቁጥር 04 እና የሳህን ማጠቢያ (Dish washer) ብዛት 01 ማሽን በብልሽት ምክንያት ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣

በህፀተ ዘናብ ግብርናና ተፈጥሮ ሃብት ኮሌጅ

በአላቂ ግምጃ ቤት

- በ2006 ዓ.ም ገቢ የሆነ ብዛት 01 overhead projector ያለአገልግሎት ተቀምጦ መገኘቱ፣
- የንብረት ገቢና ወጪ መከታተያ ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ ምዝገባ ቢኖርም በየዕለቱ ወጪና ገቢው በትክክል የማይመዘገብ መሆኑ፣

በህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

በቋሚ እና አላቂ ግምጃ ቤት

- የንብረት ወጪ ሞ/22 ሰራተኛ ባለመኖሩ ስቶክ ካርድ ምዝገባ የምትሰራ ሰራተኛ ደርባ የምትሰራ መሆኑ፣
- የንብረት ገቢና ወጪ መከታተያ ካርድ ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ ምዝገባ ቢኖርም በየዕለቱ ወጪና ገቢው በትክክል የማይመዘገብ መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ ንብረቶች ከአዳዲስ ንብረቶች ጋር ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑን ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ ባይንደር፣ወረቀት ማሸጊያ፣ስታብላይዘር፣ኤሌክትሪካል ካልኩሌተር፣ትልቁ ስቴፕላር፣ፓንቸር እና ኤክስተርናል ሃርድ ዲስክ አላግባብ የተቀመጡ መሆኑ ፣

በእንስሳት ጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣

- በእስሳት ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመድኃኒት ስቶር ውስጥ መድኃኒቶችን ለመከታተልና ለመቆጣጠር እንዲሁም ከወጪ ቀሪ የሚያሳይ ስቶክ እና ቢን ካርድ ምዝገባ ስርዓት አለመኖሩ፣

- የእንስሳት ጤና ሳይንስ ኮሌጁ የማህረሰብ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ቢሆንም የሚሸጠው የመድኃኒት ዋጋ በሚመለከተው አካል የፀደቀ የክፍያ ተመን የሌለው መሆኑ፣
- በበጀት አመቱ መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ለእንስሳት መኖ አገልግሎት የሚዉሉ የተለያዩ ግብአቶች ተገዝተው ወደ ስቶር ከገቡ በኋላ በቀን ምን ያህል መኖ እንደወጣ እንዲሁም ምን ያህል ቀሪ እንዳለ በተጨማሪም በወተት ላሞች መኖ (ፍርሽካ) እና ድርቆሽ ከስቶር ሲወጣ ምንም አይነት የምዝገባ ስርዓት የሌለው መሆኑ፣
- ሁለት የእንስሳት መኖ ስቶሮች በራቸው የተበላሸ እና መኖው ለብክነትና ለብልሹ አሰራር የተጋለጠ መሆኑ፣
- በእንስሳት ድርቆሽ ስቶር ውስጥ የጤፍ እና የሽብራ ክምችት ለመኖ ይሆናሉ ተብለው ያለ ምንም ጥቅም ከአምስት አመት በላይ ጥንቃቄ በጎደለው አያያዝ በሜዳ ለይ ተበትኖ የሚገኙ መሆኑ፣

<u>በመቐለ ኢንስቲትዩት ቴክኖሎጂ ኮሌጅ</u>

- የንብረት ምዝገባ ስቶክ ካርድ የሚሰራ ሰራተኛ ባለመኖሩ የንብረት ወጪ ማድረጊያ ሞ/22 ምዝገባ የምትሰራው ሰራተኛ ደርባ የምትሰራ መሆኑ፣
- የንብረት ገቢና ወጪ መከታተያ ካርድ ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ ምዝገባ ቢኖርም በየዕለቱ ወጪና ገቢው በትክክል የማይመዘገብ መሆኑ፣

  አገልግሎት የማይስጡ የተለያዩ ንብረቶች ከአዳዲስ ንብረቶች ጋር ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑን ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል የተለያዩ ብዛት ያላቸው መፀሃፎች፣ ፕሪንተር ቀለም፣ ፎቶኮፒ ቀለም፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ እርሳስ ማጥፊያ፣ እርሳስ መቅረጫ፣ Dis kette file፣ power supply፣ የውሃ ብርጭቆ፣ Floopy disc፣ ፎቶ ኮፒ ድራም ዩኒት፣oil filter፣ CD-ROM እና carbet science extension cleaner ያለአገልግሎት ለረጅም ዓመት የተቀመጡ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማየት ችለናል፣

2.2 <u>ተሽከርካሪዎች እና የነዳጅ አጠቃቀምን በተመለከተ</u>፣

ተሽከርካሪዎች የተገዙበት ወይም በዩኒቨርሲቲው ባለቤትነት ስር የዋሉበት ቀንና ዓ.ም በማህደራቸው ባሉ ቅጾች ላይ የሌለ መሆኑ፤ በተጨማሪም ተሽከርካሪዎቹ

በግዥ፣ በስጦታ እና በዝውውር ወደ ዩኒቨርሲቲው ሲገቡ የሞዴል19 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ኮፒ ተደርጎ በማኅደር ውስጥ ያልተያያዘ መሆኑ፣

- የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ዕለታዊ የነዳጅ፤ የዘይትና የኪ.ሜ መመዝገቢያ (ቅጽ 02)፣
- የመንግሥት ተሽከርካሪዎች ወርኃዊ የነዳጅ፤ የዘይት እና የጥገናወጪ ማጠቃለያ (ቅጽ03)፣
- የመንግሥት ተሽከርካሪዎች የነዳጅ፤ የዘይትና ቅባት መጠየቂያ (ቅፅ 08)፣ በተሽከርካሪዎች የግል ማህደር ውስጥ ያልተቀመጠ መሆኑ፣
- በጥገና ወቅት የተለወጡ ዕቃዎች የገቢ ማድረጊያ (ሞዴል19) የሚቆረጥ ቢሆንም በማህደራቸው የማይያያዝ መሆኑ፤ እንዲሁም በጥገና ወቅት የተለወጡ ዕቃዎች ሪፓርት ማቅረቢያ (ቅፅ 12) እና ከለይ የተጠቀሱት በሙሉ በማህደሩ ያልተካተቱ መሆኑ፣
- ማንኛውም የዩንቨርስቲው ተሽከርካሪዎች ታርጋ/ሰሌዳ ቁጥር አሰጣጥ ኢ..ት የሚል ሁኖ እያለ ብዛታቸው ሰባት (7) የሆኑ ትራክተሮች ሰሌዳ ቁጥር ትግ-ልዩ- 274፤ 275፤ 276፤ 278፤ 279፤ 280፤ እና 281 ለእርሻ አገልግሎት የሚውሉ ትራክተሮች ኢ.-ት የሚል ታርጋ መሆን ሲገባው ትግ-ልዩ የሚል ታርጋ የተሰጣቸው መሆኑ፣
- በመኪና የነዳጅ አጠቃቀም ስታንዳርድ /ነዳጅ በኪ.ሜ እንደ መኪናው አይነት/ ወይም ኖርማላይዜሽን በሚመለከተው መ/ቤት ያልተሰራ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

2.3 የመድኃኒት አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ

በአይደር ኮምፕረሀንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

- መድኃኒት ለተጠቃሚው መሸጥ ያለበት ከ20% ባልበለጠ የትርፍ ምጣኔ መሆን ሲገባው 25% የትርፍ ምጣኔ ከፍ በማድረግ የሚሸጥ መሆኑና የመድሃኒቶቹ ዋጋም በዝርዝርና በሚታይ መልኩ ለተጠቃሚው ያልተለጠፈ መሆኑ፣
- APTS ኦዲተብል ፋርማሲ ሲስትም የመድኃኒት ምዝገባና አያያዝ እና አጠቃቀም ሥርዓት ተግበራዊ ቢደረግም በባለሙያ መሠራት ያለባቸው ሥራዎች በባለሙያ ባለመሠራቱ ሥራው በተሟላ መልኩ ተግበራዊ እየተደረገ አለመሆኑ

በዋናው ግቢ በተማሪዎች ክሊኒክ

- የተማሪዎች ክሊኒክ የፋርማሲ ክፍል ሃላፊ ንብረት ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ምዝገባ የሚደረገው በአንድ ሰራተኛ መሆኑ፣ እንዲሁም ቢን ካርድና ስቶክ ካርድ ምዝገባ ወቅቱን ጠበቆ የማይቀናነስ መሆኑ፣
- በተማሪዎች ክሊኒክ የፋርማሲ ክፍል ውስጥ የመድሃኒቶቹ የአገልግሎት ዘመናቸው /Expiry date/ ቢን ካርድ ላይ ያልተገለፀ መሆኑ፣
- ጥቅም ላይ የማይውሉ መድኃኒቶች በአንድ መጋዘን ተለይቶ መቀመጥ ሲኖርባቸው በመድሃኒት እደላ ክፍል ውስጥ ከሌሎች አገልግሎት ከሚሰጡ መድሃኒቶች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ለጤና አስጊ በሆነ ሁኔታ የተቀመጡ መሆኑ

2.4 ልዩ ልዩ ፤

የደመወዝ ጥያቄ ክፍያ ሲቀርብ በሂሳብ ምዝገባ ማዘገዣ /JV/ የሂሳብ ምዝገባው የማይከናወን እና ባንኩ በእያንዳንዱ ሰራተኛ የቁጠባ ሂሳብ የተጣራ ደመወዝ ገቢ ማድረጉን የባንክ አድቫይስ ሲደርስ ብቻ የሂሳብ ምዝገባ የሚከናወን መሆኑን

ዩኒቨርሲቲው የዕለት ጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በየዕለቱ የማያደርግና የቆጠራው ውጤት ከሌጀር ሚዛን ጋር የማይመሳከር መሆኑ

3. የ2010 በጀት ዓመት እርምጃ ያልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ፤

- ሕግ ትምህርት ኮሌጅ ብር 58,480.00፣በማዕከል ከውስጥ ገቢ ብር 7,840.00፣በህክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ብር 92,288.00፣በሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ ከመደበኛ ብር 202,720.00፤ ከውስጥ ገቢ ብር 14,400.00፣በተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ብር 106,400.00፣በአይ.ቲ.ኤም ብር 2,520.00፣በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ብር 55,988.00፣በግብርና ኮሌጅ ብር 5,400.00፣ በአጠቃላይ ለተለያዩ ጉዳይ ለሥራ የሚመጡ እንግዳ መምህራን ከሚያገኙት ክፍያ ወይም ገቢ ላይ 30% የሥራ ግብር መቀነስ ሲገባው 2 % (ሁለት በመቶ) በመቀነሱ በልዩነት ብር 546,036.00 የስራ ግብር ያልተቀረጠ መሆኑ፤
- በሕግ ትምህርት ቤት የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ላስተማሩ ሦስት መምህራን በመንግስት ደንብና መመሪያ መሰረት ለፕሮፌሰር በክሬዲት ሃወር ብር

120 ለሌክቸር ብር 100 በማስብ መክፈል ሲገባው ለአንድ መምህር ብር 150 በማሰብ 96 ሰዓት ላስተማረበት (96*150) ብር 14,400.00 የተከፈለ ቢሆንም መከፈል የነበረበት 120*96 ብር 11,520 በልዩነት ብር 2,880.00፣ 72*150 ብር 10,800 የተከፈለ መከፈል የነበረበት 120*72 ብር 8,640.00 በልዩነት ብር 2160.00፣ 96 ክሬዲት ሃወር *150 ብር 14,400.00 ተከፈለ መከፈል የነበረበት 120*96 ብር 11,520.00 በልዩነት ብር 2880.00 ፣ በአጠቃላይ ድምር ብር 7,920.00 ከተመን በላይ ተከፈሎ መገኘቱ፤

- በኢትዮጵያ ኢንስቲትዩት ቴክኖሎጅ መቐለ ግቢ ለADHOC committee assignment በሚል ለኮሚቴ አባላት ለአንድ ሰው 600 በማሰብ ብር 4,200.00 ከውስጥ ገቢ ከደንብና ከመመሪያ ውጪ ተከፍሎ መገኘቱ፤

ፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የካቲት 2012 ዓ.ም